# የልጆች እንክብካቤ ድጋፍ መስጫ ፕሮግራም



## እንኳን ደህና መጡ

የልጆች እንክብካቤ ድጋፍ መስጫ ፕሮግራም በአሌክሳንድሪያ ውስጥ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ሁሉም ልጆች ማግኘት የሚገባቸውን ጥራት ያለው የልጆች እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ዕድሎችን ያቀርባል። ፕሮግራሙ የልጆች እንክብካቤ ወጪን ለመሸፈን የሚያግዝ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ለበርካታ ቤተሰቦች የስራ፣ የኢኮኖሚ ዋስትና እና የጤናማ ልጆች መሰረት ነው።

## ለልጆች እንክብካቤ ድጋፍ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

እባክዎ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች በየጊዜው ሊለወጡ እና የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያካትቱ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ

- ቤተሰቡ ነዋሪነቱ በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ መሆን አለበት።
- ልጆች የአሜሪካ ዜጋ መሆን አለባቸው ወይም ብቁ የሚያደርግ የቪዛ ሁኔታ ሊኖራቸው ይገባል። የወላጅ የቪዛ ሁኔታ ምን እንደሆነ ጥያቄ አናቀርብም።
- የልጆች ዕድሜ ከ13 ዓመት በታች ወይም ራሳቸውን መንከባከብ የማይችሉ ከሆነም ከ18 ዓመት በታች መሆን አለባቸው።
- ወላጆች ተቀጣሪ ወይም እውቅና ባለው ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪ መሆን አለባቸው።
- ቤተሰቡ ዝቅተኛ የደመወዝ መጠንና ከፍተኛ ወርሐዊ የገቢ ወሰኖችን ማሟላት አለበት፤ ይህም ከግብር በፊት

አንድ መስፈርቱን የሚያሟላ ቤተሰብ እስከ 72 ወራት (ስድስት ዓመት) ለሚሆን ጊዜ የልጆች እንክብካቤ ድጋፍ የሚያገኝ ሲሆን፣ ይህም በገንዘብ ድጋፍ መኖር ላይ የተመሰረተ ነው።



## እንዴት ማመልከት ይቻላል

ወደ commonhelp.virginia.gov ገብተው ማመልከቻውን በኦንላይን ይሙሉ። የኢንተርኔት አገልግሎት ለማያገኙ ወይም ማመልከቻውን ለመሙላት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች፣ በስልክ ቁጥር 703.746.5437 በመደወል ማመልከቻውን በስልክ መሙላት ይችላሉ።

## የሚገኝበት ቦታ

የልጆች እንክብካቤ ድጋፍ መስጫ ፕሮግራም አድራሻ፡ 1900 N. Beauregard Street, 2nd Floor, Suite 250, Alexandria, VA 22311. ከጽ/ቤቱ በር አጠገብ የተቀመጠ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን አለ። መደበኛ የስራ ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8 a.m.— 5 p.m. ቢሮው ክፍት መሆኑን ለማየት እባክዎን ይደውሉ።

## ለወላጆችና አገልግሎት አቅራቢዎች የሚሆን የመረጃ ምንጭ



- የማህበረሰብና ሰብአዊ አገልግሎቶች ሚኒስቴር (DCHS) | alexandriava.gov/childcare | በየሳምንቱ የሚዘምን (updated) | DCHS በእነዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ ሲሆን፣ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎችም የግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎችን ይሰራል
- Child Care Aware |  VAchildcare.org | ስልክ፡ 1.866.KIDS.TLC በመደወል ወቅታዊ የአማራጮች ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ
- Smart Beginnings | sbalexandria.org
- Child Care Microsite| childcareva.com
- Guidance for Parents | dss.virginia.gov/family/cc/publications.cgi
- Virginia Department of Social Services (DSS) dss.virginia.gov/family/cc/professionals_resources.cgi
- DSS FUSION | fusion.dss.virginia.gov/ccecd/
- USDA Child and Adult Care Food Program | fns.usda.gov/cacfp/child-day-care-centers

**የማህበረሰብ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ክፍል**

**Childcare Assistance Program**
**1900 N. Beauregard Street, 2nd Floor, Suite 250**
**Alexandria, VA 22314**

**703.746.5437 | ኢሜይል፡ dchschildcare@alexandriava.gov**